# ህዝባዊ ሰላማዊ ትግል ስንል

የኢህአዴግ መሪዎች የተያያዙት የቅልበሳ ሂደት አንዱ ጉልህ ገፅታው ግንቦትን ያስቻሉትን የፖለቲካ፣ የአስተሳሰብ፣ የተቋማት ግኝቶች እንዳልነበሩ አድርገው በማውደም በአፈናና በሽብር መጨረሻው ለማይታይ ረዥም ወቅት በህብረተሰባችን የሽግግር ክፍተት የመፍጠር ሂደት ነው። እነዚህ ፀረ ህዝብ ሃይሎች በህዝባችን ተጋድሎ ከጥፋት ሂደታቸው እንዲያፈገፍጉ ከመገደዳቸው በፊት ከእንግዲህ የህግ የበላይነት፣ የዳኝነት ነፃነት፣ ተጠያቂነት፣ የፕሬስ ነፃነት፣ የመደራጀት መብትና ነፃ ምርጫ የሚሉ ከባድ ከባድ እሴቶች ቀርቶ በቅድመ ግንቦቱ ወቅት የነበሩት የዴሞክራሲ ፍንጮች እንኳን እውን የሚሆኑበት ምንም አይነት ተአምር አይኖርም። ከዚህ አንፃር ህብረታችን ደግም ደጋግሞ ያስተጋባው ጥሪ ሁላችንም ለግንቦት ድሎች ብለን እንነሳ የሚል ነው። ይህ ማለት ግንቦትን ያስቻሉትና ዛሬ ደብዛቸው የጠፋው የዴሞክራሲ መብት ፍንጮች መልሰው እውን እንዲሆኑ መታገል ብቻ አይደለም። የኢህአዴግ መሪዎች ባሉበት የኪሳራና በህዝብ የመተፋት ደረጃ ባልተሟላ ሁኔታ እውን የነበሩ ቢሆኑም እነዚህ መብቶች እርግጥ ህዝባችን የፈለገውን እንዲመርጥ አስችለውት ነበር። ነገር ግን ድምፁን ለማስከበር ብቁ እንዳልነበሩ የዚያኑ ያህል ግልፅ ይመስለናል። ለዚህ ነው ''ለግንቦት ድሎች'' መታገል ባልን ቁጥር ''በዚያው ሂደት በነሱ ላይ መገንባት'' እያልን ትግላችን መስመር የሳተው የዴሞክራታይዜሽኑ ሂደት መልሶ በእግሩ እንዲቆምና ሂደቱ ቀጥሎ በሃገራችን ዴሞክራሲያዊ ስርአት ሰፍኖ የዚህ ሁሉ መቋጠሪያ በሆነው ነፃ ምርጫ እንዲቋጭ ሳያቋርጥ መቀጠል ያለበት ታሪካዊ ተጋድሎ ነው የምንለው።

ለዚህ ነው ከእንግዲህ ይህ ፀረ ህዝብ ስርአት በህዝብ ሃይል ተግዶ ዴሞክራሲ ከመስፈኑ በፊትና ምርጫም ከተባለ ነፃ የሆነ ቦርድ በሌለበት ሁኔታ ስለ ምርጫ ማውራት በህዝብ ትግል ማሾፍ የሚሆነው። ለዚህ ነው ከእንግዲህ ትግላችን እንደ ቅድመ ግንቦቱ ወቅት በምርጫ ዙሪያ ሳይሆን ህዝባዊ የትግል ማእበል መቀስቀስና መምራት መሆን ይኖርበታል የምንለው። ለዚህ ነው የዴሞክራሲ ፍንጮች በነበሩበት ሁኔታ እንኳን አልጋ በአልጋ ያልነበረው የዚህ ሰማእት ህዝብ ትግል ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ውስብስብና ከባድ ከባድ መስዋእትነትን የሚጠይቅ ሂደት ይሆናል የምንለው። ለዚህም ሁሉ ነው በዚህ ታሪካዊ ተጋድሎ ''እንኖርበታለን'' ብለን በህዝባችን ፊት ቃል ከገባንና ይህንን ቃላችንን ከምር ከወሰደን አይቀር ለተቀበልነው ተልእኮና ላለንበት አዲስ የትግል ምእራፍ በሚመጥን ሁኔታ የህብታችንን አወቃቀር አባል ድርጅቶች ከየድርጅት ነፃነታችን ቀንሰን ለጋራው ትግል በሚያስረክብና የስራ ቅልጥፍናን በሚያመቻች መልክ ለማሻሻል የመረጥነው።

ይህንን የዴሞክራታይዜሽን ትግል ከግቡ ለማድረስ ከፈለግን የስትራቴጂያችን ሁሉ መነሻ ግንቦት የሚልዮኖች ድል እንደነበረ ሁሉ እነዚህን ድሎች አስከብሮ ወደ ፊት ለመራመድ በግንቦት የዴሞክራሲ፣ የፍትህ፣ የህዝቦች ወንድማማችነትና የሃገር አንድነት እሴቶች ዙሪያ ሁሉም በአንድ አቅጣጫ የሚገፋበት የሚልዮኖች ትግል ያስፈልጋል የሚለው እምነት መሆን ይኖርበታል። በኛ ግምት ዛሬ ህብረተሰባችን ለሚገኝበት አስከፊ ሁኔታና ለትግሉ አደገኛ መዘረክረክ መሰረታዊው ምክንያት የኢህአዴግ መሪዎች ሆን ብለው እኛ ደግሞ በእይታ ጉድለትም ይሁን በሌሎች ምክንያቶች ግንቦት ላይ የትግሉም የድሉም ዋና ባለቤት የነበረውን ህዝባችንን ከፖለቲካው መድረክ እንዲገለል ማድረጋችን ይመስለናል። ዛሬ ከምንገኝበት አጣብቂኝ ለመውጣት ከፈለግን የኢህአዴግ መሪዎችን በአስራ አራት አመት የግፍ አገዛዛቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ተከላካይነት ህብረተሰባችንን ደግሞ ወደማያወላዳ የፖለቲካ በላይነት ያሸጋገረውን ይህንን ህዝባዊ ተሳትፎ መልሶ እውን ማድረግና ህዝባችን መልሶ የትግሉ ባለቤት መሆኑን ማረጋገጥ የስትራቴጂያችን የማእዘን ዲንጋይ አድርገን መንቀሳቀስ ይኖርብናል።

ዋናው የትግላችን አላማ ግንቦት ላይ እኛን ባኮራ፣ አለምን ባስደነቀ፣ የኢህአዴግ መሪዎችን ብርክ ባስያዘ ወኔ ህዝባችን እንደ አንድ ሰው ተንቀሳቅሶ ዴሞክራሲ በአፋኝ አገዛዝ ላይ፣ የሰላማዊ ለውጥ ሃሳብ በአመፅ ፖለቲካ ላይ፣ የህዝቦች ወንድማማችነትና የሃገር አንድነት እሴት በአናክሰህ ግዛ ርኩስ ፖለቲካ ላይ ድል ለማጎናፀፍ ያስቻለውን ህዝባዊ የትግል ማእበል መልሶ በመቀስቀስ የበጎ አዙሪት ሂደት የመክፈት አላማ ነው። ሆኖም ትኩረታችን በግንቦት

እሴቶች ዙሪያ የግንቦት ሃይሎችን በሙሉ አንቀሳቅሰን እንዴት ያኔ የተጎናፀፍነውን የማያወላዳ የፖለቲካ የበላይነት መልሰን እንያዝ የሚለው ጥያቄ ላይ መሆን ሲገባው ዛሬ በተቃዋሚው ጎራ ”ለምን እንታገል?” በሚለው ጥያቄ ሳይሆን ”እንዴት እንታገል?” በሚለው ነጥብ ላይ ልዩነቶች ሲከሰቱ እናያለን። በመካሄድ ላይ ያለው ክርክር ”ሰላማዊ ትግል ወይስ የትጥቅ ትግል?” በሚለው ጥያቄ ዙሪያ የታጠረ ቁንፅል ክርክር ይመስለናል።

በዚህ በትግል ስልት ጉዳይ አንድ በጣም ግልፅ መሆን ያለበት ቁም ነገር አለ። ዛሬ በሃገራችን አላማውን ለማራመድ ከአመፅ፣ ከሽብርና ከህገ ወጥነት ሌላ ምንም ምርጫ የሌለው አንድ ሃይል ቢኖር ህወሃት/ኢህአዴግ ብቻ ነው። የዚያኑ ያህል ደግሞ ህዝባዊ የግንቦት ሃይሎች በግንቦት እሴቶች ዙሪያ በአንድ አቅጣጫ ለመንቀሳቀስ እስከተስማሙና የህዝባችንን የትግሉ መአከልነት እስከተቀበሉ ድረስ የስልት ምርጫቸው ምንም ወሰን የሌለው ትግላቸውም በምንም ቀኖናዊነት የማይታጠር ዘርፈ ብዙና ሁለገብ ትግል እንደሚሆን ግልፅ ነው። በህዝባችን የትግሉ ማእከልነት ስምምነት ካለና ወደሱ ከተሰራ ማንም ይሁን ማን ያመቸኛል በሚለው ስልት ቢሰማራ ይህ የልዩነትና የክፍፍል ምንጭ መሆን አይኖርበትም። የህዝባችንን አጀንዳ እስካነገበ ድረስ ማንም ሃይል ”አምንበታለሁ፣ ይቻላል” በሚለው ህጋዊ ሆነ ህገ ወጥ፣ ይፋ ሆነ ህቡእ፣ ሰላማዊ ሆነ የትጥቅ ትግል መስክ ሊሰማራ የማይችልበት ምንም ምክንያት አይኖርም።

ቀስ በቀስ በግንቦት እሴቶች ዙሪያ ህዝባዊ የትግል ማእበል የመቀስቀስ አላማ የሌለው እስከሆነ ድረስ ”ሰላማዊ” የሚባለው የትግል ስልት የጥቂት ግንባር ቀደም ሃይሎች ግርግር ከመሆን አልፎ የምንፈልገውን የነፃነት ፈር አያስይዘንም። የግንቦት ሃይሎች የግንቦትን እሴቶች አንግበውና ህዝባችን የማያወላዳ የፖለቲካ የበላይነትን መልሶ ጨብጦ ከዳር ዳር በማይንቀሳቀስበት ሁኔታ የተለያዩ ሃይሎች አንዳንዴም የግንቦትን እሴቶች በሚቃረኑ የተሰበጣጠሩ ወገናዊ አጀንዳዎች እናካሂዳለን የሚሏቸው የትጥቅ ትግሎችም የትም የሚያደርሱ አይደሉም። ይህ ማለት ዛሬ ሃገራችንን በመቆጣጠር ላይ ካሉት ጦር ጠማሽና ፀረ ኢትዮጵያ ሃይሎች አንፃር ትጥቅ አንስቶ መፋለም አያስፈልግም ማለት እንዳልሆነ ግልፅ ነው። ሆኖም ከወሳኙ ህዝባዊ ተጋድሎ አንፃር እነዚህ ሃይሎች በግንቦት እሴቶች ዙሪያ ህዝባችን በሚልዮን እየተቆጠረ ለሚያካሂደው ትግል አጋዥ ሆነው ራሳቸውንም የዚህ ህዝባዊ ተጋድሎ ”የታጠቀ ክንፍ” አድርገው ካልተንቀሳቀሱና አልፈው ተርፈው ደግሞ ይህንን ህዝባዊ ተጋድሎ ”እንተካለን” ብለው የሚግደረደሩ ከሆነ የትም እንደማያደርሱ ግልፅ መሆን ይኖርበታል።

ነገሩ እንዲህ ሆኖ ሳለ ዛሬ በተቃዋሚው ጎራ በአንድ በኩል ”ለሰላማዊ ህጋዊ ትግል” ቆመናል በሚሉና በሌላ በኩል ”ያለ ትጥቅ ትግል ስርየት የለም” በሚሉ ወገኖቻችን መሃከል የሚንፀባረቀው ልዩነት ዋናውንና ወሳኙን ህዝባዊ ተጋድሎ ወደ ጎን ትቶ የሚካሄድ ክርክር ሆኖ ይታያል። የህብረታችን በሶስተኛ መደባዊ ሸንጎው ”ህዝባዊ ሰላማዊ” የትግል ስልት የመከተል አላማ እንዳለው የገለፀው እየተካሄደ ባለው ክርክር ’የተረሳውን” የህዝባዊ ተሳትፎና የህዝባችን የትግሉ ባለቤትነት ጉዳይ መልሶ የስትራቴጂያችን ማእከል ለማድረግ ካለው ፅኑ አቋም በመነሳት ነው። በኛ እምነት ሰላማዊና ህዝባዊ የሚሉት ቅፅሎች በምንም አይነት ተነጣጥለው የሚታዩ አይደሉም። ሰላማዊ ትግል ህዝብን ካልያዘ በአየር ላይ የሚንሳፈፍና ለህወሃት/ኢህአዴግ ”እድሜ ቀጣይ” ስልት ከመሆን አያልፍም። ህዝብ ከዳር ዳር እንደ አንድ ሰው ሆኖ ለአንድ አላማ በማይንቀሳቀስበት ሁኔታ ደግሞ ዛሬ ሃገራችን በምትገኝበት ውስጣዊ፣ የአካባቢና አለም አቀፍ የተወሳሰበ ሁኔታ ለህዝባችን ተጋድሎ በአጋዥነት ያልተሰለፈ የትጥቅ ትግል ብቻውን የተወሳሰበውን ሁኔታ ይበልጥ ያወሳስባል እንጂ መፍትሄ የሚያመጣ አይሆንም።

ከዚህ ትንተና ተነስተን ዛሬ የሃገራችን ዴሞክራቶች ሊጠቀሙባቸው ከሚችሉት ከአሸዋ የበዙ ስልቶች አንፃር በምንም ቀኖናዊነት ሳይታጠሩ ህዝብን አንቀሳቅሶ ታግሎ የማታገል ስትራቴጂ ለመንደፉ ጉዳይ ቅድሚያ ሰጥተው መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል እንላለን። እንዲህ አይነቱ የትግል ስትራቴጂ እጅግ አስቸጋሪና ውስብስብ እንደሆነና ከፍተኛ መስዋእትነትም እንደሚጠይቅ ግልፅ ነው። እውን እንዲሆን ከፈለግን ደግሞ አንደኛ ህዝባችንን በምን በምን አጀንዳዎች ዙሪያ ”ተነስ” እንበለው? ሁለተኛ ደግሞ በዚህ መልክ የምንቀሰቅሰው ህዝባዊ ትግል እስከድል ድረስ ቀጣይነት እንዲኖረው ምን ምን መስራት አለበት የሚሉትን ሁለት ጥያቄዎች መመለስ ያስፈልጋል።

ለሰላማዊ ህዝባዊ ትግል ህዝባችንን በምን አጀንዳ እናንቀሳቅሰው? በደርዘን ሽህ የሚቆጠሩ ዜጎችን ለእስራት፣ ለግድያ፣ ለስደት፣ ለእንግልትና ይህ ነው ለማይባል ወከባ የዳረገው አንባገነንና ሽብርተኛ አገዛዝ በመፈፀም ላይ

ያለው ግፍ ምን ያህል ዘግናኝ ቢሆንና ምን ያህል ክቡር የሆነ መስዋእ-ትነት እየተከፈለበት ቢሆንም የግንቦትን ቅልበሳ
መዘዞች በዚህ በፖለቲካው ገፅታው ወስኖ ማየት ትልቅ ስህተት ይሆናል። የግንቦት ቅልበሳ ሌላው ዋና ገፅታና መዘዝ
ከህዝብ ድምፅ ዝርፊያው በተጓዳኝ በኢኮኖሚና ማህበራዊ መስኮች የተደረገውን "የህዝባዊ አማራጭ ዝርፊያ" የሚ
መለከት ነው። ህብረታችንም ሆነ ቅንጅቱ በምርጫው ዘመቻ ወቅት የኢህአዴግን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፖሊሲዎች
በሃገር አውዳሚነት ፈርጀው፣ በህዝብ ፊት ከኢህአዴግ መሪዎች ጋር ተከራክረው ለህዝባችንና ለሃገራችን ይበጃሉ ባ
ሏቸው በጎ አማራጭ ፖሊሲዎች ዙሪያ ተንቀሳቅሰዋል። ህዝባችንም የተሻለ ቀን ያመጡልኛል ብሎ በማመን ለነዚህ
አማራጮች ድምፁን ሰጥቷል። የኢህአዴግ መሪዎች በሸፍጥ አሸነፍን ሲሉ በሸብር ሊያንበረክኩት በሚፈልጉት ህብረ
ተሰብ ላይ ምንም አይነት ተጠያቂነት በሌለበት ሁኔታ በእነዚህ አጥፊ ፖሊሲዎች እንቀጥላለን ማለታቸው እንደሆነ ግ
ልፅ ነው። በዚህም የተነሳ ዛሬ በግልፅ እንደሚታየው በደርዘን ሚልየን የሚቆጠሩ ዜጎች በየቀኑ እየከፋ ለሚሄድ እር
ዛት እየተዳረጉ ናቸው። ምንም አይነት እርምጃ የሚቻለው ይህንን የቅልበሳውን ድርብ ገፅታ ተገንዝበን በፖለቲካው
መስክ ብቻ ሳይሆን በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎችም ዙሪያ ህዝባችንን ይዘን ስንንቀሳቀስ ብቻ ነው። ይህ ካልተ
ደረገ ሸብርና የአመራር ክፍተት ተጋግዘው ግራ ባጋቡት ህብረተሰብ ውስጥ እነዚህ ቀውሶች እየተባባሱ ቀጥለው በበር
ካታ የአፍሪካ አገሮች እንደሚታየው ሃገራችን በግልፅ አማራጮች ዙሪያ ሳይሆን ህልውናዋን ሳይቀር ጥያቄ ውስጥ ሊያ
ስገቡ ለሚችሉ እጅ እግር ለሌላቸው ትርምሶች ልትዳረግ የምትችልበት አደጋ እንዳለ ግልፅ መሆን አለበት።

እስካሁን የሃገራችንን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ለመፍታት የተደረገው ትግል ዘርፈ ብዙ በሆነ መልኩ ሳይሆን
ግንጥል በሆነ በፖለቲካ መስክ ብቻ ያተኮረ እንደነበረ ግልፅ ነው። በቅድመ ግንቦቱ ወቅት የነበረውን የትግል ልምዳ
ችንን ብንመለከት የምናየው ይህንን ነው። በነዚህ አመታት የህዝባችንን ጉረሮ አንቀው የያዙትን የሰማይ ስባሪ የሚያክ
ሉ የህልውና ቀውሶች ወደ ጎን ትተን የዳኝነት ነፃነት፣ የህግ የበላይነት፣ ነፃ ፕሬስ፣ የመደራጀት መብት፣ የተቋማት ግ
ንባታ.... ወዘተ እያልን በነዚህ ክቡር እሴቶች ዙሪያ ከፍተኛ መስዋእትነት የጠየቀ ትግል ስናካሂድ ቆይተናል። የዚያኑ
ያህል ደግሞ ትግሉ እነዚህን ሁሉ እኔም አምንባቸዋለሁ ብቻ ሳይሆን በተግባርም እያዋልኳቸው ነው እያለ ከሚመፃደቅ
የጥፋት ሃይል ጋር ስለነበረ ይህ ሁሉ ምንም የጠራ የፖለቲካ የበላይነት ያላጎናፀፈን የአህያ ውድቂያ ትግል ሆኖ እንደ
ቆየ ግልፅ ነው። ከቅልበሳውና ከተከፈለው መስዋእትነት ባሻገር የግንቦት ድልና ታሪካዊነት ቀጣዩ ትግል እንዳለፈው በ
ፖለቲካው መስክ ከመታጠር አልፎ ሊሄድ የሚችልበትን ሁኔታ ማመቻቸቱ ነው ብለን እናምናለን።

በፖለቲካው መስክ ግንቦት ማን በሃቅ ማን ደግሞ በልፈፋ ደረጃ ለዴሞክራሲያዊ እሴቶች እንደቆመ ለህ
ዝባችንም ለአለም አቀፍ ኮሙኒቲውም በግልፅ አሳይቶ የህወሃት/ኢህአዴግን መሪዎች እርቃን ያስቀረ ለሃገራችን ዴሞ
ክራሲያዊ ሃይሎች የማያወላዳ የፖለቲካ የበላይነት ያስጨበጠ ሂደት ነበር። ሁለተኛ ህዝባችንን በማዋከብ ላይ ያሉት
በርካታ የህልውና ችግሮች ከጅምላ ስራ አጥነት፣ እስከ መናጢ ድህነት፣ ከትውልድ ገዳዩ የትምህርት ፖሊሲ እስከ
ኤችአይቭ ኤይድስ፣ ርሃብ ፈልፋይ ከሆነው ፀረ ድሃ ገበሬ ፖሊሲ ነጋዴው በሃቅ ነግዶ፣ ኢንቬስተሩ በተረጋጋ ሁኔታ
ገንዘቡን አውጥቶ ለራሱም ለሃገሩም እንዳይሰራ እጅ ከወርች አስሮ እስከያዘው አድላዊና ሙሰኛ አሰራር በአጭሩ በሃገ
ር ኪሳራ ጥቂቶች ለጥቂቶች መበልፀግ የደነገጉትን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ስርአት በማጋለጥ ሰፊ ዘመቻ ተካሂዷል
። ዛሬ በዚህ እምርታ ቀጥለን የቅልበሳውን መዘዞች በሙሉ ፊት ለፊት ከመግጠም ይልቅ ይህንን ድርብ ግኝት የትም
በትነን እንደ ቅድመ ግንቦቱ ዘመን ዛሬም ተመልሰን በፖለቲካው ግንጥል ትግል ጎዳና እየተሰማራን እንገኛለን። የተያዘ
ው የሰዶ ማሳደድ ስትራቴጂ እነዚህን ሚልዮኖች እየተቀጡባቸው ያሉ ከባድ ከባድ ቀውሶች ከገፈት ቀማሹ ህዝብ ጋ
ር አብሮ የመዋጋት ስትራቴጂ ሳይሆን ግፋንና መከራውን "ለቀባሪ ለማርዳት" በሚግደረደሩ መግለጫዎች "በማጋለጥ"
የተወሰነ አካሄድ ነው። ይህንን "የፍየል በወዲህ ቅምዝምዝ በወዲያ" የሚመስል አጓጉል አካሄድ እየያዝን ያለነው በ
ህብረተሰባችን ላይ በመውረድ ባለው አፈናና ሸብር በመዋከብ ላይ በመሆናችን ብቻ አይደለም። ከዚህ ይልቅ መሰረታ
ዊ የሆነ የእይታ ችግር ያለብን ይመስለናል።

የመጀመሪያ ችግር የህዝባችንን ተጨባጭና የህልውና ጥያቄዎች "በይደር" ለማስቀመጥ የሚታየው አባ
ዜ ነው። ለዚህም የሚቀርበው ክርክር ደግሞ ተደግሞ ተሰምቷል። እናውቀዋለን። ይኸውም " ዛሬ ዋናው ተግባር ለዴ
ሞክራሲና ለዴሞክራሲ ተቋማት ግንባታ የሚደረገውን ትግል ማፋፋም ነው። ከዚያ ዴሞክራሲ ሰፍኖ ነፃ ምርጫ ሲደ

ረግ ሁሉም አማራጭ ፕሮግራሙን ይዞ ህዝብ ፊት መቅረብ! ይችላል" የሚል ክርክር ነው። እነዚህ ችግሮች ከዴሞክራሲው ትግል ድል ባሻገር ይደረስባቸዋል በሚል ስሌት በግንቦት የምርጫ ዘመቻ ወቅት እንግበን የተንቀሳቀስንባቸው አማራጭ ሰነዶች ገና ዘንቦ ተባርቆ የሚደረግ ነፃ ምርጫ ሲመጣ በሚል እጉል ስሌት ጨርሶ ተረስተው "የክት ቀን" ሰነዶች ሆነዋል። የኛ ተጋድሎ እናቱም አባቱም የምርጫ ሰሞን ግርግር ይመስል።

ከዚህ ተያይዞ እንዲህ አይነቱን አጓጉል አካሄድ ለመደገፍ የሚቀርብ ሌላም ክርክር አለ። ይኸውም ያለንበት ስርአት መሰረታዊና የዝቅተኛም ዝቅተኛ የሚባሉ መብቶችን እንኳን ረግጦ የያዘ በመሆኑ " ስራ ለስራ አጡ"፣ " ምግብ ለተራበው"፣ "መናጢ ድህነት በቃን" "የአካባቢ ውድመት ምድራችንን እያጠፋ ነው" ......ወዘተ እየተባለ የሚካሄድ ትግል ጨርሶ "የሚፈቅድ" ስላይደለ መጀመሪያ እንዲህ አይነት ትግል "ለሚቻልበት" ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንታገል የሚል አስገራሚ ክርክር ነው። እርግጥ የአለንበት ስርአት ማንኛውንም ህዝብን ይዞ የሚነሳ ጥያቄ ከለየለትና በአመፅ መደምሰስ ካለበት "የነውጠኞች ሴራ"፣ ማንኛውንም ህዝብ ይዞ የሚካሄድ ሰላማዊና ህጋዊ ተጋድሎ "ህገ መንግስታዊውን ስርአት በአመፅ ለማፍረስ" ከሚደረግ እንቅስቃሴ ለይቶ ማየት የማይችል እጅግ ኋላ ቀር የሆነ ስርአት ነው። ከዚህ እውነታ ተነስተን ግን ላለንበት አስቸጋሪ ሁኔታ የሚመጥን ስትራቴጂ ነድፈን እንንቀሳቀሳለን እንላለን እንጂ "ለዴሞክራሲያዊ ስርአት እንዳንታገል ፀረ ዴሞክራሲያዊው ስርአት አስቸገረን ወይም አይፈቅድም" ብለን ማቆም አንችልም። ዞሮ ዞሮ ደግሞ የህወሃት/ኢህአዴግ መሪዎች ፈቀዱት አልፈቀዱት በህዝብ ብሶቶችና ጭንቀቶች ዙሪያ ህዝብን ይዘን እስካልታገልን ድረስ በጎ ራእይ ብቻ አንግቦ በሚካሄድ ትግል እነዚህን የህዝብ ጥያቄዎች ለማስተናገድ የሚያስችለን "ዴሞክራሲያዊ ስርአት" እናመጣለን ማለት አደገኛ የሆነ የህልም አለም ውስጥ መኖር ነው።

ህብረታችን ህዝባዊ ሰላማዊ ትግል ሲል አንደኛ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ብሶታቸውን አንግበው ለችግራቸው መፍትሄ ለመሻት እንዲታገሉ መቀስቀስ ያስፈልጋል ማለቱ ነው። ሁለተኛ እነዚህ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ተራ በተራ መነሳታቸው ተራ በተራ ከመመታት የማያልፍ እጉል መስዋእትነት እንዳይሆን ሁሉም "ብሶትህ ብሶቴ" በሚል መንፈስ በትግግዝና በአንድነት እንዲነሱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል ማለት ነው። ሶስተኛ በዚህ መልክ የሚንቀሳቀሱት የህብረተሰብ ክፍሎች ዛሬ የሚገኙበት ከባድ ቀውስ የግንቦት ቅልበሳ መዘዝ እንደሆነ እንዲገነዘቡና ማንኛውም ዘላቂነት ያለው መፍትሄ ከኢህአዴግ መንግስት ከስልጣን መወገድና ዴሞክራሲ በሰፈነበት ሁኔታ በህዝብ ፊት ተጠያቂ የሆነ መንግስት መመስረት እንደሆነ አውቀው እዚያው በዚያው ለዴሞክራሲ ስርአት እንዲታገሉ መቀስቀስ ያስፈልጋል። ይህንን ተግባር ለመፈፀም እንዲቻል የሃገራችን ዴሞክራቶች ሁለት ነገሮችን ማሟላት ይኖርባቸዋል።

አንደኛ ህዝባችንን ለእንደዚህ አይነቱ ዘርፈ ብዙ ተጋድሎ "ተነስ" ብለን ተደማጭነት ለማግኘት ከፈለግን መጀመሪያውኑ ተቃዋሚዎች ግንቦት ላይ የነበራቸውንና ዛሬ በተደጋጋሚ በተፈፀሙ ስህተቶች የተነሳ የትም የበተኑትን ተአማኒነት መልሰው መገንባት ይኖርባቸዋል። ህዝባችን አንዴ ሰልፉ ውጣ ተብሎ ወዲያው ደግሞ ያ ሰልፍ ተሰርዟል ሲባል፣ አንዴ ቀትር ላይ ለቤት መዋል አድማ ተሰናዳ ተብሎ ለዚህ ጥሪ ተግባራዊነት ሲሰናዳ ማምሻው ላይ መሪ ተብየዎቹ ከባእዳንና ከነአቶ መለስ ተመሳጥረው አድማው ተሰርዟል ብለው ሲያረዱት፣ አንዴ አገራዊ ጉባኤ ተብሎ ከሰባት መቶ በላይ የሚሆኑ ታጋይ ዜጎች ከሃገሪቱ አራት ማእዘናት አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ "አዳራሽ ጠፋ" በሚል ተልካሻ ሰበብ ጉባኤው ተሰርዞ ሁሉም አንገቱን ደፍቶ ወደ መጣበት እንዲመለስና የኢህአዴግ ጨካኝ ካድሬዎች ጥርስ ውስጥ እንዲገባ ሲደረግ የታዘበ ህዝብ ነው። እንዲህ አይነቱ የመመሪያዎች ዥዋዥዌ ታጋዩን ህዝብ ግራ እንዳጋባና በመሪዎቹም ላይ የነበረው አመኔታ እንዲሟሸሽ እንዳደረገው ግልፅ ነው። ይህ አልበቃ ብሎ ትላንት የድርጅት አጥር ሳያግዳቸው እጅ ለእጅ ተያይዘው ለትግሉ አመራር ይሰጡ የነበሩ ሃይሎች ዛሬ በትንሹም በትልቁምና ዞሮ ዞሮ ከህዝባችንንና ሃገራችን ችግሮች አንፃር "እዚህ ግቡ" ሊባሉ በማይችሉ ልዩነቶች ሲከፋፈሉ ማየቱ መሪዎች የነበራቸውን ተአማኒነት ገደል እንዳስገባው አለመረዳት ራስን ማታለል ብቻ ይሆናል። ከዚህ ይልቅ የህዝባችንን ተጋድሎ እንመራለን የሚሉ ሃይሎች ይህንን ሃቅ ተገንዝበው በአንድ በኩል "በአንድነት ተነስ" በሚሉት ህዝብ ፊት ራሳቸው አንድ ሆነው በመቆም በሌላ በኩል ደግሞ ጥራት ብቻ ሳይሆን ፅናት ያለው አመራር ለመስጠት በመሞከር የፈራረሰውን ተአማኒነት መልሰው መገንባት ይኖርባቸዋል።

ይህንን ህዝባዊ ተጋድሎ ለመምራት በዚህ መልክ ግንቦት ላይ የነበረውን ተአማኒነት መልሶ መገንባት ብ
ቻ አይበቃም። የአመራር ቀጣይነትም ሊታሰብበት የሚገባው ቁልፍ ጥያቄ ነው። ግንቦት ላይ እነ አቶ መለስ "እንከን የ
ለሽ" ምርጫ እናካሂዳለን ብለው መለፈፋቸው፣ ህዝባችን እየተሰዋም እየተንገላታም ቢሆን በሰላም ለምድር አንቀጥቅ
ጥ ሰላማዊ ሰልፎች መውጣት መቻሉ፣ ህዝባዊ ስብሰባዎች ከምላ ጎደል ያለችግር መካሄዳቸው፣ ተቃዋሚዎች ከመን
ግስት "እኩል ቤት ገብተው" በህዝብ ፊት መከራከር መቻላቸው፣ ፕሬሱ ከምላ ጎደል የህዝብ ልሳንነቱን አረጋግጦ መ
ንቀሳቀስ መቻሉ.....ይህ ሁሉ ለትግላችን ከወዲሁ ዴሞክራሲ በሰፈነበት ስርአት ውስጥ የሚካሄድ "ስልጡን" ገፅታ ሰጥ
ቶ አጉል መዘናጋት እንደፈጠረ ዛሬ ግልፅ ይመስለናል። በዚህ መዘናጋት የተነሳ ከግንባር ቀደሙ ሃይል የተወሰነው ክፍ
ል "ችግር ቢመጣስ?" በሚል የጥንቃቄ አካሄድ ይፋ ከመውጣት ተቆጥቦ ፀረ ህዝቦቹ ሊደርሱበት የማይችሉት ጠንካራ
መዋቅር እንዲገነባ ጥረት አልተደረገም። በዚህም የተነሳ መሪዎቹ ከያለበት ተለቅመው ሲታፈሱ ህዝባችን በተለይ ደ
ግሞ ወጣቱ የረባ መሪና አቀነባባሪ ሃይል አጥቶ ትግሉን በደመ ነፍስን፣ በግብታዊነትና በተበታተነ ሁኔታ ለማካሄድ ተገ
ዶ የከፈለውን መስዋእትነት ሁላችንም እናውቀዋለን። ቀጣይነት ያለው አመራር ስንል ከዚህ ህዝባችን አይከፍሉ መስዋ
እትነት እንዲገብር ካደረገው ስህተት ተምረን ሰላማዊና ህዝባዊ ትግላችን የሚያስፈልገውን ቀጣይነት ያለው አመራር
እውን ለማድረግ በጥንቃቄ የሚገነባ መዋቅር የግድ ያስፈልገናል ለማለት ነው።

ይህ ተአማኒነት መልሶ የመገንባቱና የትግሉን አመራር ቀጣይነት የማረጋገጡ ተግባርዛሬ በተቃዋሚው ጎ
ራ የተሰለፉ የዴሞክራሲና የአንድነት ሃይሎች በሙሉ የጋራ ተልእኮ ነው። ህብረታችን ካለፉት ድሎችም ሆኑ ውድቀ
ቶች ትምህርት በመቅሰም ብቻ ሳይሆን ካለንበትም ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት ለዚህ የጋራ ተልእኮ መሳካት በበኩሉ የ
ሚያደርገውን አስተዋፅኦ ለማጎልበት አስፈላጊ ናቸው ያላቸውን የአወቃቀርና የአሰራር ለውጦች አድ-ርጓል። ሆኖም በ
ግንቦት እሴቶች ዙሪያ ህዝባችንን አንቀሳቅሶ የቅልበሳውን መዘዞች እየተቋቋሙ ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመሸጋገ
ር የሚደረገው ተጋድሎ የግንቦት ዴሞክራሲያዊና አገር ወዳድ ሃይሎች ታሪካዊ ተልእኮ መሆኑን አሁንም በአፅንኦት ለ
ማስረገጥ ይወዳል። ከዚህም በመነሳት ለቀጣዩ ዘርፈ ብዙና ውስብስብ ትግል የዚች አገር ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ሃይሎ
ች በጋራ መክረውና ዘክረው የጋራ ስትራቴጂ ለመንደፍና የጋራ የሆነ ታግሎ የሚያታግል መድረክ ለመፍጠር እንዲች
ሉ ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ ባረግነው ጥሪ መሰረት አንድ አገር አቀፍ የቀውጢ ግዜ ግብረ ሃይል ስለሚቋቋምበት ሁኔ
ታ ለመምከር ፈቃደኛ ከሆኑ ወገኖች ጋር የምክክርና የዝግጅት (steering committee)
ለመፍጠር ከመቸውም ጊዜ ይበል-ጥ ዝግጁ መሆኑን ለማብሰር ይፈልጋል።